NON-TECHNICAL SUMMARY

Prepared for Local Stakeholder Consultations organized in the Federal Democratic Republic of Ethiopia for

"ECC_Multi-country Electric Clean Cooking Programme"

Date: September 2026

Table of Contents

LIST OF ACRONYMS 4
NON-TECHNICAL SUMMARY 5
Introduction 5
Purpose and technology of the Project 5
Target Group and Location 6
Project Technology 6
Implementation plan 9
Carbon credits 9
Motivation and Benefits of the Project 9
Environmental Benefits: 10
Contribution to Sustainable Development Goals (SDGs) 11
Compliance With Safeguards Principles 12

LIST OF ACRONYMS

CO – Carbon Monoxide

CO_2 – Carbon Dioxide

GHG – Greenhouse Gas

GMOs – Genetically Modified Organisms

IAP – Indoor Air Pollution

LSC – Local Stakeholder Consultation

NOx -Nitrogen Oxides

SOx- Sulfur Oxides

N_2O Nitrous Oxide

CH4 Methane

PM -Particulate Matter

PD – Project Developer

SDG – Sustainable Development Goal

CME – Coordinating Managing Entity

IoT - Internet of Things

kWh- Kilowatt-hour

MECD- Metered & Measured Energy Cooking Devices

CP- Crediting Period

Introduction

BURN Manufacturing Co, its affiliates and related entities (BURN), is pleased to announce Local Stakeholder Consultation ("LSC") meetings for its planned projects in the Federal Democratic Republic of Ethiopia These projects will be housed under the "ECC_Multi-country Electric Clean Cooking Programme".

BURN Manufacturing Co, its affiliates and related entities (BURN) recognizes the evolving cooking energy needs and requirements across Ethiopia. In response, BURN has designed these planned carbon assets to accelerate the adoption of modern, electric, and metered cooking appliances, thereby reducing the country's dependence on non-renewable biomass.

Purpose and technology of the Project

The Federal Democratic Republic of Ethiopia remains highly dependent on non-renewable biomass, primarily wood and charcoal, to meet domestic cooking needs. This reliance has significant environmental consequences, including deforestation, land degradation, loss of soil fertility, reduced water retention capacity, and increased greenhouse gas (GHG) emissions. In addition, the incomplete combustion of biomass in traditional cookstoves generates harmful indoor air pollutants that are associated with serious health conditions such as pneumonia, stroke, ischemic heart disease, chronic obstructive pulmonary disease, and lung cancer.

The project Activity will generate significant emissions reductions and expand access to modern, clean cooking technologies by distributing highly efficient electric induction cookstoves to electrified households which satisfy the baseline scenario description across Ethiopia. These will contribute to end-user and community co-benefits and the Sustainable Development Goals (SDGs).

This project, for which the LSCs are planned, will be implemented by the Coordinating Managing Entity (CME) of the proposed project, BURN Manufacturing Co, its affiliates and related entities (BURN). The electric cooking appliances will be sourced from BURN Manufacturing Co. ("BURN").

BURN is Africa's leading clean cooking company, headquartered in Westlands, Nairobi, with its manufacturing factory and research and development hub in Ruiru, Kenya. BURN has distributed over 7.5 million clean cookstoves across the continent, impacting over 38.2 million lives and saving 48.4 million tons of wood. In Kenya, BURN has distributed over 1.5

million stoves, including more than 21,000 electric stoves. The company has the capacity to produce over 250,000 stoves monthly and employs over 1,500 people in Kenya, half of whom are women.

Target Group and Location

The Project targets households in peri-urban and urban areas that rely on biomass and fossil fuels for cooking and use their stoves mainly for domestic cooking purposes. Carbon subsidies enable BURN Manufacturing Co, its affiliates and related entities (BURN), to offer affordable clean cooking solutions to the households. Accordingly, BURN Manufacturing Co, its affiliates and related entities (BURN), aims to replace traditional, inefficient biomass stoves with cleaner cooking solutions, reducing or eliminating the use of non-renewable biomass fuels in the project scenario.

Project Technology

The projects in Ethiopia may accommodate different electric and metered stove types manufactured by BURN or other manufacturers and include within their target end-users. The Induction Cooker is integrated with an Internet of Things (IoT) sensor which allows remote monitoring of kWh usage, significantly improving carbon credit integrity through accurate calculation of emission reductions. The technology also enables Pay as you cook financing, making the stove more affordable. Usage and power usage data are relayed to BURN's proprietary Nexus software, which enables the customer experience team (Call Centre) and local field agents to support customers and solve issues.




Figure 1: Illustration of useful heat delivery mechanism - Induction Cookers



Figure 2: ECOA Induction Cookstove with Stainless Steel pot

Electrical Specifications	
Description	**Value/Naming**
Power rating	200W -2000W
Voltage rating	220VAC- 250VAC
Nominal Current rating	8 Amps

Implementation plan

- Local Stakeholder Consultations – Q4 2026
- Stakeholder Feedback Round- Q4 2026
- Stove distributions– Approximately 1,000,000 stoves by end of first Crediting period.

Local Stakeholder Consultations (LSC) are planned for three dates in three different locations across Ethiopia.

14th of Dec 2026; Jigjiga, Universal Hotel – Somali Region

16th of Dec 2026, Adama, Melka Adama Hotel – Oromia region
18th of Dec 2026, Hawassa, Golden Gate Hotel, Sidama region

Local stakeholders invited to participate include non-governmental organizations, women groups, research institutes and organizations/individuals working on topics related to the project activity, policy makers on a national and state level as well as local people, communities and/or representatives who are directly or indirectlyaffected by the project.

-

In case of any questions or if you want further details and project information prior to the consultation, please give a call to Rashid Abdi Garane, BURN LSC Consultant in Ethiopia,

(+251 92 910 2980).

Carbon credits

Greenhouse gas (GHG) emission reductions are achieved by displacing the non-renewable biomass (firewood and charcoal) used for cooking in the baseline with electric cooking. These fuel savings will be calculated as avoidance of carbon credits using the stated MECD v2 methodology and applicable certification rules and procedures. The revenues from the sale of carbon credits help amongst others to:

a. Distribute improved cooking devices at a subsidized price affordable for the end users

b. Scale up and expand the Project, thus reaching a wider range of end-users.

c. Generating more jobs.

d. Provide a reliable after-sales service.

e. Sensitize and raise end-users' awareness about the benefits and how to use the improved cookstoves.

COMMUNITY BENEFIT SHARING IN ETHIOPIA
Introduction
Carbon financing is vital in increasing access to clean and improved cooking solutions. By providing up-front subsidies, carbon projects like BURN increase the affordability of high-quality stoves. BURN's clean cookstove projects are designed so that a significant share of the carbon finance benefit reaches the community upfront, in the form of a subsidy on the purchase price of the stove. Families then continue to benefit financially throughout the project through reduced household spending on cooking fuel, in addition to improved health outcomes, time savings and other co-benefits. With project developers and investors bearing most of the project costs and risks, end users (communities) receive a substantial share of the carbon benefit.

Carbon Benefit
BURN creates value for communities in Ethiopia in the following ways:
Stove subsidies

BURN makes high-quality, fuel-efficient stoves and uses carbon finance to offer communities a substantial subsidy on each stove. This compares favorably with other cookstove carbon projects and means that the end user (community) receives a meaningful share of the carbon benefit from day one, at no risk to them.
Community Savings
The high thermal efficiency of BURN stoves means that families cook with much less fuel. An independent randomized controlled trial conducted by the University of Chicago and the University of Pennsylvania found that households using improved stoves significantly reduce

their yearly spending on cooking. Over the project's lifetime, these savings, together with the upfront subsidy, add up to a significant financial benefit for each household.

Improved Health and Gender Outcomes
Families spend considerably less time cooking and collecting fuel. This is time women and girls can reinvest in employment, education or leisure. In addition, BURN stoves substantially reduce indoor air pollution, leading to improvements in self-reported health outcomes.

Community Empowerment
All BURN projects offer ongoing community engagement and training. Local women and girls are supported to transition to clean cooking, learn about modern fuels and gain employment in our projects.

Local Employment
BURN creates local employment opportunities in Ethiopia and is in the process of formally incorporating its local legal entity, BURN Ethiopia. Once established, the entity will oversee all in-country operations, including legal, finance, distribution and commercial functions.

Capacity Building
BURN invests strongly in skills development, including comprehensive training in data enumeration, data reporting, sales prospecting, customer experience, and carbon monitoring. In addition to these transferable skills, we are building a manufacturing and operations workforce in our assembly facility.

Case Study : Electric induction project
Electric projects are slightly different because the cost of the ECOA induction stove package, which includes a set of cookware, is higher, and families benefit from access to a pay-as-you-go (PAYGO) financing plan.

At present, carbon revenue is used to subsidies the overall cost of the stove and reduce repayment times. In future, it could also be used to provide electricity subsidies, lowering ongoing cooking costs and helping families make the switch from charcoal to electric cooking.

Community share of the benefit: Carbon benefits can reach households at several points in the project: at the point of sale, during the PAYGO repayment period, and after repayment through support with electricity costs. As with cookstove projects, communities realize a large part of the value of the project, while investors are repaid gradually over the project's lifetime.

About BURN

In our projects, carbon revenues and benefits are shared between the end user (community), the project developer (BURN) and the investor. As BURN’s projects are pre-financed by investors, a significant portion of the carbon credits issued goes directly to the investor as repayment. This means that, depending on the contract, BURN retains only a

limited share of the carbon revenue.

BURN is a mission-driven social business, and any carbon revenue it retains is reinvested in:

R&D for innovative new products

Providing subsidies for more families

Growing our Impact

Next Steps

The specific level of stove subsidy, the share of carbon benefit reaching communities and the expected household savings will be presented and discussed with communities, local government and partners during the local stakeholder consultation, so that the final benefit-sharing arrangement reflects local needs and priorities

Motivation and Benefits of the Project

The project stoves reduce the consumption of non-renewable biomass, and in so doing, improve critical socio-economic outcomes including health and financial savings for beneficiaries.

Baseline indoor air pollution associated with combusting non-renewable biomass is related to diseases including pneumonia, stroke, ischemic heart diseases, chronic obstructive pulmonary diseases, and lung cancer.

Environmental Benefits:

The Project is designed to significantly reduce dependence on non-renewable biomass for household energy needs associated with cooking, previously supplied by traditional and/or inefficient cookstoves, thus reducing deforestation connected to cooking biomass fuel. In addition, the reduction of the use of non-renewable biomass for cooking will lead to a reduction in emissions such as NOx, SOx, particulate matter PM2.5, CO, thus improving indoor air quality. Usage of the devices under this project will aid in reducing the emission of GHG gases associated with global warming including Carbon dioxide, Methane and Nitrous oxide CO2, CH4 & N2O.

Contribution to Sustainable Development Goals (SDGs)



Besides reducing GHG emissions in line with the United Nations Sustainable Development Goal (SDG) number 13 'Climate Action', the project will also seek to increase other long-term sustainability benefits for the local families as well as the local environment. Projects are expected to contribute to different Sustainable Development Goals (SDGs) in the following ways:

- Reduction in end-user expenses related to the purchase of fuel for cooking (in line with **SDG 1 'No Poverty')**.
- Less harmful carbon monoxide and particulate matter during combustion in households will reduce indoor air pollution and thereby decrease of respiratory diseases, headaches, and itchy eyes, particularly for women and children who spend lot of their time in cooking activities (in line with S**DG 3 'Good health and well-being').**
- The implementation of the project will require the CME to provide specialized training in sales, monitoring and end-user engagement (in line with **SDG 4 'Quality Education')**
- Time savings are associated with fuel purchases and cooking, thus more time is available, for other tasks, like income generating activities or for growing food (in line with **SDG 5 'Gender Equality**').
- Increased penetration of modern, clean and efficient cooking technologies (in line with **SDG 7 'Affordable and Clean Energy**')
- The Induction Cooker stoves will be sourced from BURN's manufacturing facility located in Kenya, thus generating hundreds of jobs on the African continent.

Other jobs are created for sales, marketing, distribution, and monitoring staff in Ethiopia. (In line with **SDG 8 'Decent Work and Economic Growth**')

• Reduced deforestation and forest degradation in areas where non-renewable biomass is used as a source of fuel. This will contribute to the overall stability of forest ecosystems which support biodiversity, watersheds, and soil conditions (in line with SDG 15 'Life on Land')

https://www.un.org/sustainabledevelopment/sustainable-development-goals/

Compliance With Safeguards Principles

The project will follow the approved Safeguarding Principle and Requirement to ensure that the project does not undermine or conflict with any national, sub-national or local regulations for fuel supply/household cooking. A high-level summary of compliance is provided below:

Social Principles

•Principle 1: Human rights:

The distribution of improved cooking devices or any activities related to the operation of the projects, has minimal risk of contravening any human rights laws or international Social Principles (version 2.1) of the Gold Standard for Global Goals. The project, as such, is not in violation of Ethiopian Constitution, international treaties and conventions ratified by Ethiopia or any other regional Zones, Woredas or national laws on the protection and sanctity of human rights

. **•Principle 2: Gender equality and Women's Empowerment:**

The use of efficient devices in substitution or reduction of traditional woody biomass will generate specific outcomes that benefit and respect women's rights. Individual benefits, and an assessment of baseline conditions in the pre-project scenario, shall be provided for each LSC as a requirement to SDG 5 claims as intended in the Project.

•Principle 3: Community Health and Safety:

There are no real or perceived negative community health outcomes envisaged for the project activities. The CME shall ensure that all projects (through the respective LSCs and Design Documentation) define and communicate compliance with all safeguards associated with health and safety working conditions including assessments that protect

the health and safety of people employed for the operation of the project.

. •Principle 4: Cultural Heritage, Indigenous Peoples, Displacement and Resettlement: The project is defined by the installation of portable cooking devices, so there is no risk that the project activities implementation will affect any cultural heritage sites. Each LSC will walk stakeholders through project specific safeguards to protect against:

- •Alteration, damage, or removal of any sites, objects, or structures of significant cultural heritage Sites of cultural and historical heritage
- •Forced eviction and displacement
- •Land tenure and other rights
- •The rights of Indigenous people

•Principle 5: Corruption:

The CME shall ensure that all projects demonstrate and communicate to stakeholders that corruption and corrupt practices of any kind shall not be tolerated in the implementation of project.

Economic Principles

•Principle 6 – Economic Impacts:

The CME will not tolerate the use of forced labor or engage in any employment practices that violate international and national labor laws. The project must demonstrate and communicate to stakeholders all safeguards and compliance with the provisions of Principle 6 of the Safeguarding Principles Requirements.

Environmental and Ecological Principles

Principle 7: Climate and Energy

•**Emissions:** The project will decrease GHG emissions from the baseline scenario over a period of up to 15 years (project duration with 2 CP renewals). Using the project's cookstoves will help avoid the emissions of many tons of CO2 in the atmosphere.

• **Energy supply:** The objective of this project is to implement improved technologies that use less non-renewable biomass or that do not use non-renewable biomass at all. So intrinsically, the quantity of wood taken from natural resources is reduced compared to the baseline scenario.

Principle 8: Water

• **Impact on Natural Water Patterns/Flows:** The project will not have any negative impact on the water resources in the region. There will be no meaningful change in the volume of water available for consumption by households.

• **Erosion:** The project reduces notably fuelwood consumption and thus protects the natural forest cover. Therefore, the possibility of erosion will indirectly be reduced, and water stability will be enhanced.

Principle 9: Environment, Ecology and Land Use:

• **Landscape Modification and Soil:** No crops or other products will be produced in the project.

• **Vulnerability to Natural Disasters:** There will be no impact by the project on natural disasters. The project will not lead to any land use changes and will have no impact on the land within the project area. No exacerbation of natural or human-caused hazards can therefore be expected.

• **Biosafety and Genetic Resources:** No GMOs will be used in the project. • Release of pollutants: Due to the project activities fuelwood consumption is expected to be reduced, and no fossil fuel is expected to be burned, there is no risk of releasing pollutants to the environment.

• **Hazardous and Non-hazardous Waste:**

The cookstoves are manufactured at BURN's own facility in Kenya, in compliance with Kenyan health, safety and environmental regulations. In Federal Democratic Republic of Ethiopia, Project activities are limited to distribution, sales, repair and monitoring by locally recruited staff, generating only limited non-hazardous waste (packaging, replaced parts, damaged stoves). This is managed through the Project's repair and waste management strategy, which prioritizes repair, reuse and recycling, with staff trained and equipped for safe handling in line with SDG 8.

• **Pesticides and Fertilizers:** The project does not involve the application of pesticides and fertilizers.

• **Harvesting of Forests:** The project will reduce fuel wood demand and thus also the harvest rate of forests. Therefore, the project has a positive impact on the forest cover

. • **Food security:** The project does not impact on the growth of food nor the quality of the food.

• **Animal welfare:** The project does not involve animal husbandry.

• **High Conservation Value Areas and Critical Habitats**: The project will be required

to demonstrate safeguards and compliance with national and international protocols on critical habitats and biodiversity.

- **Endangered Species:** The project is not envisaged to have any impact on their habitat as it only affects existing households.
- **Invasive alien species:** The project will not introduce any alien species.

Contact Information:

For feedback/suggestions / Partnership Contact:

Abdirahman Yusuf

Carbon PM Horn of Africa

Abdirahman.yusuf@BURNmfg.com

(Project Representative)

ቴክኒካዊ ያልሆነ ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለሚካሄደው የአካባቢ ባለድርሻዎች ምክክር (Local Stakeholder Consultation) የተዘጋጀ ጥሪ

ለ

«ECOA_BURN ብዙ-ሀገራዊ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ፕሮግራም»

መግቢያ

በርን ማኑፋክቸሪንግ (BURN Manufacturing) ለ«ECOA_BURN ብዙ-ሀገራዊ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ፕሮግራም» የአካባቢ ባለድርሻዎች ምክክር (LSC) ስብሰባዎችን ማስታወቅ ይወዳል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለቤት ውስጥ ምግብ ማብሰያ ፍላጎት ታዳሽ ባልሆኑ የባዮማስ ሀብቶች (ማለትም በማገዶ እንጨትና በከሰል) ፍጆታ ላይ ከፍተኛ ጥገኝነት አላት። የቤተሰብ የባዮማስ ፍጆታ በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ያስከትላል። እነዚህም የደን መጨፍጨፍ፣ የመሬት መራቆት፣ የአረንጓዴ ሐውስ ጋዞች (GHG) ልቀት፣ እንዲሁም የአፈር ለምነትና ውሃን የመያዝ አቅም መቀነስን ያካትታሉ።

በተጨማሪም፣ ማገዶ እንጨትና ከሰል በሚቃጠሉበት ወቅት የሚለቀቁ ጤናን የሚጎዱ ብክለቶች የቤት ውስጥ አየር ብክለትን (IAP) ያስከትላሉ። ይህም እንደ የሳንባ ምች፣ ስትሮክ፣ በልብ ጡንቻ ደም አቅርቦት መጓደል የሚከሰት የልብ ሕመም፣ ሥር የሰደደ የሳንባ መዘጋት በሽታ (COPD) እና የሳንባ ካንሰር ያሉ በሽታዎችን ሊያስከትል ይችላል።

የፕሮጀክቱ አላማ እና ቴክኖሎጂ

BURN Manufacturing Co. እንዲሁም ተባባሪ እና ተዛማጅ ድርጅቶቹ (በአጠቃላይ BURN) «ECOA_BURN ባለብዙ ሀገራት የንጹህ ምግብ ማብሰያ ፕሮግራም» በሚል ፕሮግራም ሥር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የካርቦን ፕሮጀክት ተግባራትን ያከናውናሉ።

«ECOA_BURN ባለብዙ ሀገራት የንጹህ ምግብ ማብሰያ ፕሮግራም» ስር የሚካተት እያንዳንዱ መደበኛ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለሚገኙ ቤተሰቦች ከፍተኛ የውጤታማነት ደረጃ ያላቸውን የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች (ICS) ማሰራጨት ነው። ይህም እንደ ምግብ ቤቶች ያሉ በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚካሄዱ አነስተኛ የንግድ ሥራዎች እነዚህን ምድጃዎች የሚጠቀሙ ቤተሰቦችንም ያካትታል።

በባህላዊ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች ውስጥ ባዮማስ (ማገዶ) ሙሉ በሙሉ ባለመቃጠሉ ምክንያት ካርቦን ዳይኦክሳይድን ጨምሮ የተለያዩ የአረንጓዴ ሐውስ ጋዞች (GHGs) ይለቀቃሉ። ለፕሮጀክቱ የተነደፉት የተሻሻሉ የምድጃ ቴክኖሎጂዎች (ICS) ከመሠረታዊ ባህላዊ ምድጃዎች

ጋር ሲነጻጸሩ የሙቀት ማስተላለፍ ውጤታማነታቸው የተሻለ ነው። በዚህም በመሠረታዊ ሁኔታ (baseline scenario) ተመሳሳይ የኃይል መጠን ለማግኘት ቤተሰቦች የሚጠቀሙትን ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) መጠን ይቀንሳሉ።

ይህ የማገዶ ፍጆታ መቀነስ የአረንጓዴ ሐውስ ጋዞች (GHGs) እና የቤት ውስጥ አየር ብክለት (IAP) ልቀቶችን ለመቀነስ መሠረት ይሆናል። በተጨማሪም ማገዶን ለመሰብሰብ እና/ወይም ለመግዛት የሚወጣውን ጊዜና ገንዘብ በመቀነስ በቤተሰብ ኑሮ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ተጠቃሚዎች የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን (ICS) በመጠቀም፣ ከካርቦን ክሬዲቶች ጋር የተያያዙ መብቶቻቸውን በሙሉ የፕሮጀክቱ አስተባባሪና አስተዳዳሪ አካል (Coordinating and Managing Entity) ሆነው ለተሰየሙት ለበርን ማኑፋክቸሪንግ ኩባንያ (BURN Manufacturing Co.) እና ለተባባሪና ተዛማጅ ድርጅቶቹ ይመድባሉ፤ ያስተላልፋሉም።

የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች (ICSs) በፕሮጀክቱ የተወሰነ የተግባር ክልል ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች በቀጥታ በመሸጥ እና/ወይም በማሰራጨት ይቀርባሉ።

በርን (BURN) በአፍሪካ ቀዳሚ የንጹህ ምግብ ማብሰያ መፍትሄዎች አቅራቢ ድርጅት ሲሆን፣ ዋና መሥሪያ ቤቱ በኬንያ ናይሮቢ ዌስትላንድስ (Westlands) ይገኛል። የማምረቻ ፋብሪካውና የምርምርና ልማት ማዕከሉ ደግሞ በኬንያ ሩይሩ (Ruiru) ይገኛሉ።

BURN በአፍሪካ ውስጥ ከ7.5 ሚሊዮን በላይ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን ያሰራጨ ሲሆን፣ ከ38.2 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን በአዎንታዊ መልኩ ነክቷል፤ 48.4 ሚሊዮን ቶን የሚጠጋ የእንጨት ፍጆታንም ለማስቀረት አስችሏል።

በኬንያ ብቻ ከ1.5 ሚሊዮን በላይ ምድጃዎችን ያሰራጨ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ከ21,000 በላይ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ይገኙበታል። ድርጅቱ በወር ከ250,000 በላይ ምድጃዎችን የማምረት አቅም ያለው ሲሆን፣ በኬንያ ከ1,500 በላይ ሠራተኞችን ቀጥሮ ያሠራል። ከእነዚህ ሠራተኞች ግማሾቹ ሴቶች ናቸው።

ዒላማ ቡድን እና የፕሮጀክቱ ቦታ

የዚህ እንቅስቃሴ ዋነኛ ዒላማ ቡድን የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን (ICS) ከመቀበላቸው በፊት ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) በመጠቀም በባህላዊ ምድጃዎች ላይ ምግብ የሚያበስሉ የከተማ፣ የከተማ ዳርቻ እና የገጠር ቤተሰቦች ናቸው። ይህም የዒላማ ቡድኑን ከፕሮጀክቱ በፊት ያለውን መሠረታዊ ሁኔታ (Baseline Scenario) ያመለክታል።

የፕሮጀክቱ የተግባር ወሰን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚገኙት 12 ክልሎች እና 2 ቻርተርድ ከተሞች (Chartered Cities) ውስጥ የሚገኙ የከተማ፣ የከተማ ዳርቻ እና/ወይም የገጠር አካባቢዎችን ያካትታል።

ቴክኖሎጂ

ፕሮጀክቱ የተለያዩ የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን (ICS) ሞዴሎች ሊያሰራጭ ይችላል። እነዚህ የICS ሞዴሎች ከፍተኛ የአጠቃቀም ውጤታማነት እንዲኖራቸው የተነደፉ ሲሆን፣ ዲዛይናቸውም በፕሮጀክቱ አካባቢ ያለውን የአካባቢውን የምግብ አሠራር ባህል ከግምት ውስጥ ያስገባል። ይህም በቴክኖሎጂ የሚመጡ መሻሻሎችና የኑሮ ደረጃ ማሻሻያዎች ባህላዊ አጠቃቀሞችንና ልማዶችን ሳይጎዱ እንዲተገበሩ ያስችላል።

ፕሮጀክቱ በጊዜ ሂደት ሌሎች የምድጃ ሞዴሎችንም ለማሰራጨት ሊወስን ይችላል።



ኢኮላ-ከሰል



ኢኮላ-እንጨት

የምርት ስፔሲፊኬሽኖች		
መለኪያ	ኢኮላ-ከሰል	ኢኮላ-እንጨት
የሙቀት ውጤታማነት (Thermal Efficiency)	71.3%	53.7%

የማብሰያ ሃይል መጠን (ኪሎዋት)	0.956kW	1.228kW
የPM2.5 በጠቅላላ የተሰጠ ኃይል (mg/MJd)	38.16 mg/MJd	210.2 mg/MJd
CO በጠቅላላ የተሰጠ ኃይል (g/MJd)	3.78 g/MJd	5.50 g/MJd
የደህንነት ነጥብ	90%	97.5%

የአፈጻጸም እቅድ

የተሻሻሉ የከሰል ምድጃዎችን ማሰራጨት በ2027 ዓ.ም. ይጀምራል። በመጀመሪያው የካርቦን ክሬዲት ማመንጫ ጊዜ (Crediting Period) መጨረሻ ድረስ በድምሩ 4,000,000 የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች (ICSs) ይሰራጫሉ ተብሎ ይገመታል፤ ከእነዚህም 2,000,000 የከሰል ምድጃዎች እና 2,000,000 የእንጨት ምድጃዎች ናቸው።

የአካባቢ ባለድርሻ አካላት ምክክሮች (LSC) በኢትዮጵያ በሦስት የተለያዩ አካባቢዎች በሦስት የተለያዩ ቀናት እንዲካሄዱ ታቅዷል።

ቦታ 1፡ ጅጅጋ፣ የሶማሌ ክልል – ኢትዮጵያ

መሰብሰቢያ ቦታ፡ ዩኒቨርሳል ሆቴል

ቀን፡ ህዳር 5፣ 2019 ዓ.ም. (ዲሴምበር 14፣ 2026 እ.ኤ.አ.)

ቦታ 2፡ አዳማ፣ የኦሮሚያ ክልል – ኢትዮጵያ

መሰብሰቢያ ቦታ፡ መልካ-አዳማ ሆቴል

ቀን፡ ህዳር 7፣ 2019 ዓ.ም. (ዲሴምበር 16፣ 2026 እ.ኤ.አ.)

ቦታ 3፡ ሀዋሳ፣ የሲዳማ ክልል – ኢትዮጵያ

መሰብሰቢያ ቦታ፡ ጎልደን ጌት ሆቴል

ቀን፡ ህዳር 9፣ 2019 ዓ.ም. (ዲሴምበር 18፣ 2026 እ.ኤ.አ.)

ካርቦን ክሬዲቶች

ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) ፍጆታን በመቀነስ የሚገኙ የአረንጓዴ ሐውስ ጋዞች (GHGs) ልቀት ቅነሳዎች በማረጋገጫ (Certification) ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት ወደ ካርቦን ክሬዲቶች ይቀየራሉ። ከካርቦን ክሬዲቶች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ከሌሎች ጥቅሞች በተጨማሪ የሚከተሉትን ለመደገፍ ይውላል፦

- የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን ለዋና ተጠቃሚዎች ተመጣጣኝ በሆነ ድጎማ የተደረገበት ዋጋ ማቅረብ፤
- ፕሮግራሙን ማሳደግና ማስፋፋት፣ በዚህም ለበለጠ ቁጥር ላላቸው ዋና ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፤
- ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር፤
- በምርምርና ልማት (R&D) ላይ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በማድረግ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምድጃዎች በዝቅተኛ ወጪ ማምረት፤
- አስተማማኝ የድጎረ-ሽያጭ አገልግሎት መስጠት፤
- ዋና ተጠቃሚዎችን ስለተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች ጥቅሞችና አጠቃቀም ማስገንዘብ እና ግንዛቤያቸውን ማሳደግ።

በኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጥቅም ማካፈያ

መግቢያ

ካርቦን ፋይናንስ ንጹህና የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ መፍትሔዎችን ተደራሽነት ለማሳደግ ወሳኝ ሚና አለው። አስቀድሞ ድጎማ በማቅረብ፣ እንደ BURN ያሉ የካርቦን ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምድጃዎች ለተጠቃሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገኙ ያደርጋሉ።

የBURN ንጹህ የምግብ ማብሰያ ፕሮጀክቶች ከካርቦን ፋይናንስ የሚገኘው ጥቅም ከፍተኛ ድርሻ ከፕሮጀክቱ መጀመሪያ ጀምሮ በምድጃው የግዢ ዋጋ ላይ በሚደረግ ድጎማ መልክ በቀጥታ ለማኅበረሰቡ እንዲደርስ ታስቦው የተነደፉ ናቸው።

ቤተሰቦች በፕሮጀክቱ ቆይታ ወቅትም ለምግብ ማብሰያ ነዳጅ የሚያወጡት ወጪ በመቀነሱ በገንዘብ ይጠቀማሉ። ከዚህም በተጨማሪ የጤና

ሁኔታ መሻሻል፣ ጊዜ መቆጠብና ሌሎች ተጨማሪ ጥቅሞችን ያገኛሉ።

የፕሮጀክት አስፈጻሚዎችና ኢንቨስተሮች አብዛኛውን የፕሮጀክቱን ወጪና ተያያዥ ስጋቶች የሚሸከሙ በመሆናቸው፣ ዋና ተጠቃሚዎች (ማኅበረሰቦች) ከካርቦን ፋይናንስ ጥቅሙ ከፍተኛ ድርሻ ያገኛሉ።

የካርቦን ጥቅም

BURN በኢትዮጵያ ለሚገኙ ማኅበረሰቦች እሴት የሚፈጥርባቸው መንገዶች እንደሚከተለው ናቸው፡-

የምድጃ ትርፎች

BURN ከፍተኛ ጥራት ያላቸውንና ነዳጅ ቆጣቢ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን ያመርታል። በተጨማሪም ካርቦን ፋይናንስን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ምድጃ ግዢ ለማኅበረሰቡ ከፍተኛ የዋጋ ድጎማ ያቀርባል። ይህ አሠራር ከሌሎች የምድጃ ካርቦን ፕሮጀክቶች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ጥቅም ያለው ሲሆን፣ ዋና ተጠቃሚዎች (ማኅበረሰቡ) ከካርቦን ፋይናንስ ጥቅሙ ትርጉም ያለው ድርሻ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ያለምንም የገንዘብ ስጋት እንዲያገኙ ያስችላል።

የማኅበረሰብ ቁጠባ

የBURN ምድጃዎች ከፍተኛ የሙቀት ውጤታማነት ስላላቸው፣ ቤተሰቦች ምግብ ለማብሰል እጅግ ያነሰ ነዳጅ ይጠቀማሉ። በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ እና በፔንሲልቬንያ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደ ገለልተኛ የዘፈቀደ ቁጥጥር ያለው ሙከራ (Randomized Controlled Trial) የተሻሻሉ ምድጃዎችን የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ለምግብ ማብሰል የሚያወጡትን ዓመታዊ ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚቀንሱ አረጋግጧል። በፕሮጀክቱ የሥራ ዘመን ውስጥ እነዚህ የወጪ ቁጠባዎች ከመጀመሪያው የምድጃ ግዢ ድጎማ ጋር ሲደመሩ፣ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ጉልህ የሆነ የገንዘብ ጥቅም ያስገኛሉ።

የተሻሻሉ የጤና እና የፆታ ውጤቶች

ቤተሰቦች ምግብ ለማብሰልና ማገዶ ለመሰብሰብ የሚያጠፉት ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል። ሴቶችና ልጃገረዶች ይህንን ተጨማሪ ጊዜ ለሥራ፣ ለትምህርት ወይም ለመዝናኛ ሊያውሉት ይችላሉ። በተጨማሪም የBURN ምድጃዎች የቤት ውስጥ አየር ብክለትን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳሉ፤ ይህም በተጠቃሚዎች በራሳቸው በሚያቀርቡት የጤና ሁኔታ ሪፖርት ላይ መሻሻል እንዲታይ ያደርጋል።

የማኅበረሰብ አቅም ግንባታ

ሁሉም የBURN ፕሮጀክቶች ቀጣይነት ያለው የማኅበረሰብ ተሳትፎና ሥልጠና ያቀርባሉ። በአካባቢው የሚገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች ወደ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ዘዴዎች እንዲሸጋገሩ፣ ስለ ዘመናዊ ነዳጆች እንዲማሩ እና በፕሮጀክቶቻችን ውስጥ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

የአካባቢ ሥራ ዕድል

BURN በኢትዮጵያ የአካባቢውን የሥራ ዕድሎች ይፈጥራል፤ በተጨማሪም BURN Ethiopia የተሰኘውን የአገር ውስጥ ሕጋዊ አካል በይፋ ለማቋቋም በሂደት ላይ ይገኛል። ይህ አካል ከተቋቋመ በኋላ፣ በኢትዮጵያ የሚከናወኑትን ሁሉንም ሥራዎች፣ የሕግ፣ የፋይናንስ፣ የስርጭትና የንግድ ሥራዎችን ጨምሮ፣ ይቆጣጠራል።

የአቅም ማጎልበቻ

BURN ለክህሎት ልማት ከፍተኛ ትኩረትና ኢንቨስትመንት ያደርጋል። ይህም በመረጃ ስብስብ፣ በመረጃ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ በሽያጭ ዕድሎች ፍለጋ፣ በደንበኞች አገልግሎት ልምድ እና በካርቦን ክትትል ላይ የሚሰጥ አጠቃላይ ሥልጠናን ያካትታል። ከእነዚህ በተለያዩ የሥራ መስኮች ሊያገለግሉ ከሚችሉ ክህሎቶች በተጨማሪ፣ BURN መገጣጠሚያ ፋብሪካው ውስጥ የማምረቻና የሥራ ከንውን ሠራተኞችን እየሰለጠነና እያበቃ ነው።

ጉዳይ ጥናት 1፡ የተሻሻለ ምግብ ማብሰያ ፕሮጀክት

የምድጃ ካርቦን ፕሮጀክት ዋና ዋና የትግበራ ደረጃዎች እንደሚከተለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡-

- BURN ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምድጃዎች ይነድፋል።
- BURN ለዋና ተጠቃሚው የሚደርሰውን የምድጃ አጠቃላይ ወጪ ትልቅ ድርሻ ለመሸፈን ከኢንቨስተሮች የካርቦን ፋይናንስ ያሰባስባል። ይህ ወጪ የምድጃ ማምረቻን፣ ስርጭትን፣ የፕሮጀክት አስተዳደርና አፈጻጸምን እንዲሁም የካርቦን ሥራዎችን ያካትታል።
- BURN የተሻሻሉ ምድጃዎችን ለቤተሰቦች በከፍተኛ ድጎማ በተደረገበት ዋጋ ያሰራጫል።
- ቤተሰቦች በአዲሶቹ ምድጃዎች ምግብ ያበስላሉ፤ በዚህም የነዳጅ ፍጆታቸውን በመቀነስ የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀት ቅነሳዎችን ያስገኛሉ።
- BURN የካርቦን ክሬዲቶችን ያረጋግጣል። ከክሬዲቶቹ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ለኢንቨስተሮች የተዋዋሉትን ገንዘብና የካፒታል ወጪያቸውን ለመመለስ ይውላል። ቀሪው ገቢ ደግሞ የፕሮጀክቱን ቀጣይ ወጪዎች ለመሸፈን፣ ለምርምርና ልማት (R&D) እንዲሁም ተጨማሪ ቤተሰቦችን ለመድረስና የፕሮጀክቱን ተጽዕኖ ለማሳደግ የፕሮጀክቱን ሥራዎች ለማስፋፋት ይውላል።

የማኅበረሰቡ የጥቅም ድርሻ፡-ድጎማው ምድጃው ለተጠቃሚው በሚረከብበት ጊዜ የሚቀርብ በመሆኑ፣ ማኅበረሰቡ ከፕሮጀክቱ የሚገኘውን የጥቅም ከፍተኛ ድርሻ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ያገኛል። ከዚያም በፕሮጀክቱ የሥራ ዘመን በሙሉ የነዳጅ ፍጆታንና የሚያጠፋውን ጊዜ በመቆጠብ ተጨማሪ ጥቅም ያገኛል። እነዚህ ቁጠባዎች ከመጀመሪያው የምድጃ ግዢ ድጎማ ጋር ሲደመሩ፣ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ጉልህ የሆነ የገንዘብ ጥቅም ያስገኛሉ።

ስለ BURN

በፕሮጀክቶቻችን ውስጥ ከካርቦን የሚገኙ ገቢዎችና ጥቅሞች በዋና ተጠቃሚዎች (ማኅበረሰቡ)፣ በፕሮጀክት አልሚው (BURN) እና

በኢንቨስተሩ መካከል ይከፋፈላሉ። የBURN ፕሮጀክቶች በኢንቨስተሮች ቅድመ ፋይናንስ የሚደረግላቸው በመሆኑ፣ ከሚወጡት የካርቦን ክሬዲቶች ከፍተኛ ድርሻ የኢንቨስተሩን ገንዘብ ለመመለስ በቀጥታ ለኢንቨስተሩ ይመደባል። ይህም በውሉ ውሎች መሠረት BURN ከካርቦን ገቢው የተወሰነ ውስን ድርሻ ብቻ የሚይዝ መሆኑን ያመለክታል።

BURN በማኅበራዊ ተልዕኮ የሚመራ የንግድ ድርጅት ሲሆን፣ ከካርቦን ገቢ ውስጥ የሚያስቀረውን ማንኛውንም ድርሻ እንደገና በሚከተሉት ዘርፎች ላይ ኢንቨስት ያደርጋል፦

- አዳዲስና ፈጠራዊ ምርቶችን ለማበልጸግ በምርምርና ልማት (R&D) ላይ፤
- ለተጨማሪ ቤተሰቦች ድጎማ ለማቅረብ፤
- የፕሮጀክቱን ተጽዕኖ ለማሳደግ።

ቀጣይ ደረጃዎች

የእያንዳንዱ ምድጃ የድጎማ መጠን፣ ከካርቦን ጥቅሙ ለማኅበረሰቡ የሚደርሰው ድርሻ እና ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ይጠበቃል የተባለው የወጪ ቁጠባ በአካባቢያዊ ባለድርሻ አካላት ምክክር ወቅት ለማኅበረሰቦች፣ ለአካባቢ መንግሥት አካላት እና ለአጋሮች ቀርቦ ይወያይበታል። ይህም የመጨረሻው የጥቅም ክፍፍል ሥርዓት የአካባቢውን ፍላጎቶችና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እንዲያንጸባርቅ ያስችላል።

ዲጂታል ክትትል፣ ሪፖርቲንግ እና ማረጋገጫ (DMRV)

በካርቦን ክሬዲት አመንጪነት ሂደት ውስጥ ግልጽነትን፣ ትክክለኛነትንና ተጠያቂነትን ለማሳደግ፣ ፕሮጀክቱ በሰፊ ልኬት የዲጂታል ክትትል፣ ሪፖርት አዘገጃጀትና ማረጋገጫ (DMRV) ሥርዓትን ይተገብራል።

የDMRV ሥርዓቱ የዲጂታል መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን፣ የጂኦ-መለያ አሰጣጥን (Geotagging)፣ በደህንነቱ በተጠበቀ የክላውድ መድረክ ላይ የተመሠረቱ የመረጃ ቋቶችን እና የተዋቀሩ የክትትል ፕሮቶኮሎችን በመጠቀም የምድጃ ስርጭትን፣ የተጠቃሚዎችን መረጃ እና የምድጃ አጠቃቀምን (ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ) ይከታተላል። የመስክ መረጃ ሰብሳቢዎች መረጃን በሞባይል መሣሪያዎች ይሰበስባሉ። ይህም በወረቀት ላይ በተመሠረቱ ሥርዓቶች ምክንያት የሚፈጠሩ ስህተቶችን በመቀነስ የመረጃውን ትክክለኛነትና ታማኝነት ያሻሽላል።

የDMRV ማዕቀፉ የሚከተሉትን በማድረግ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማክበር ሂደትን ያጠናክራል፦

- የተሰራጩ ምድጃዎችን ከስርጭታቸው ጀምሮ ለመከታተል ያለውን አቅም ማጠናከር፤
- ሪፖርት የሚደረጉ የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀት ቅነሳዎችን ታማኝነት ማሻሻል፤
- የመረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲከማችና ለአዲት ዝግጁ እንዲሆን መደገፍ፤
- ለባለድርሻ አካላት ያለውን ግልጽነት ማሳደግ።

የDMRV ውህደት ክትትሉን ብቃት ያሻሽላል እና በፕሮግራሙ ስር ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን እምነታማ ካርቦን ክሬዲቶችን ማውጣትን ይደግፋል።

ለዘላቂ የልማት ግቦች (SDGs) አስተዋጽኦ



ይህ ፕሮጀክት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 13ኛው ዘላቂ የልማት ግብ «የአየር ንብረት እርምጃ» (Climate Action)[1] ጋር በተጣጣመ መልኩ የአረንጓዴ ሐውስ ጋዝ (GHG) ልቀትን ከመቀነሱ በተጨማሪ፣ ለአካባቢው ቤተሰቦችና ለአካባቢ ጥበቃ የረጅም ጊዜ ዘላቂ ጥቅሞችን ለማሳደግ ይጥራል።

[1] https://www.un.org/sustainabledevelopment/sustainable-development-goals/

በዚህ ፕሮግራም ሥር የሚከናወኑ የፕሮጀክት ተግባራት ለተለያዩ ዘላቂ የልማት ግቦች (SDGs) እንደሚከተለው አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፦

- **ለድህነት ቅነሳ (SDG 1 – «ድህነትን ማጥፋት»)፦** ዋና ተጠቃሚዎች ለምግብ ማብሰያ ነዳጅ ግዢ የሚያወጡትን ወጪ መቀነስ።

የቤተሰብ የነዳጅ ወጪ በቤተሰብ በጀት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ሊኖረው ይችላል። ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) ፍጆታን መቀነስ ከፍተኛ የገንዘብ ቁጠባ ያስገኛል። ቤተሰቦችም ያጠራቀሙትን ገንዘብ ለሌሎች ጠቃሚ ዓላማዎች ሊያውሉት ወይም እንደ ቁጠባ ሊያስቀምጡት ይችላሉ።

• **ለጤናና ደኅንነት (SDG 3 – «ጤናማ ሕይወትና ደኅንነት»)፦** በቤተሰብ ደረጃ በማቃጠል ሂደት የሚለቀቁትን ካርቦን ሞኖክሳይድና ጥቃቅን ብናኝ ቅንጣቶች መቀነስ የቤት ውስጥ አየር ብክለትን ይቀንሳል። በዚህም የመተንፈሻ አካል በሽታዎችን፣ ራስ ምታትንና የዓይን ማሳከክን ይቀንሳል። ይህ በተለይ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በምግብ ማብሰል ሥራ ላይ ለሚያሳልፉ ሴቶችና ልጆች ጠቃሚ ነው።

• **ለፆታ እኩልነት (SDG 5 – «የፆታ እኩልነት»)፦** የተሻሻሉ ምድጃዎች ውጤታማ ዲዛይን የምግብ ማብሰያ ጊዜን ያሳጥራል፤ እንዲሁም ነዳጅ የመግዛት ተደጋጋሚነትን ይቀንሳል። ይህም በተለይ ነዳጅ በመሰብሰብና ምግብ በማዘጋጀት ረገድ እውቅና የማይሰጠውን የሥራ ጫና ለሚሸከሙ ሴቶችና ልጃገረዶች ጊዜ ይቆጥባል። ያገኙትንም ተጨማሪ ጊዜ ለሌሎች ጠቃሚ ተግባራት ሊያውሉት ያስችላቸዋል።

• **ለተመጣጣኝ ዋጋ ያለውና ንጹህ ኃይል (SDG 7 – «ተመጣጣኝ ዋጋ ያለውና ንጹህ ኃይል»)፦** ፕሮጀክቱ ንጹህ፣ ዘመናዊና ውጤታማ የምግብ ማብሰያ ቴክኖሎጂዎችን የማግኘት ዕድልን ያሰፋል።

• **ለጥራት ያለው ትምህርት (SDG 4 – «ጥራት ያለው ትምህርት»)፦** የሽያጭ ወኪሎችና የመረጃ ሰብሳቢዎች ስለተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች አጠቃቀም፣ ስለሚያስገኙት የኢኮኖሚ ጥቅሞችና ስለአካባቢ ጥቅሞቻቸው ልዩ ሥልጠና ያገኛሉ።

• **ለተገቢ የሥራ ዕድልና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት (SDG 8 – «ተገቢ የሥራ ዕድልና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት»)፦** የፕሮጀክቱ ትግበራ ምድጃዎችን በማሰራጨት፣ በመሸጥና ለደንበኞች ድጋፍ በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች የሥራ ዕድሎችን ይፈጥራል።

• **ለምድራዊ ሕይወትና ሥነ-ምህዳር (SDG 15 – «በምድር ላይ ያለ ሕይወት»)፦** የተሻሻሉ ምድጃዎችን በመጠቀም የሚገኘው የነዳጅ ቁጠባ በአፍሪካ ውስጥ ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) ፍላጎትን በአጠቃላይ ይቀንሳል። ይህም ከደን ጭፍጨፋ ጋር የተያያዘውን ጫና ለመቀነስ ያግዛል።

ከመከላከያ መርሆዎች (Safeguards) ጋር ተገዢነት

ፕሮጀክቱ ከነዳጅ አቅርቦትና ከቤተሰብ የምግብ ማብሰያ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ብሔራዊ፣ ከብሔራዊ በታች ያሉ የአስተዳደር እርከኖች ወይም አካባቢያዊ ደንቦችን እንዳያዳክም ወይም እንዳይጋጭ፣ ዓለም አቀፍ የጥበቃ መርሆንና መስፈርቶችን ይከተላል።

የተገዢነት አጠቃላይ ማጠቃለያ ከዚህ በታች ቀርቧል፦

ማኅበራዊ መርሆዎች

መርህ 1፡ ሰብዓዊ መብቶች፦ የተሻሻሉ የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎችን ማሰራጨት ወይም ከፕሮግራሙና ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ማንኛውም ተግባራት የሰብዓዊ መብቶች ሕጎችን፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ወይም በጥበቃ መርሆዎቹ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተያያዥ ድንጋጌዎች የመጣስ አደጋ እጅግ ዝቅተኛ ነው። በብሔራዊ ደረጃ በሚካሄደው የአካባቢ ባለድርሻ አካላት ምክክር (LSC) ወቅት፣ CME እያንዳንዱ አስተናጋጅ አገር በክልላዊና በብሔራዊ ደረጃ ያወጣቸውን ሕጎችና ደንቦች፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያጸደቃቸውን የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎችና ደንቦች በሰፊው ይገመግማል፤ የግምገማውንም ውጤት ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል።

መርህ 2፡ የፆታ እኩልነትና የሴቶችን አቅም ማጎልበት፦ ባህላዊ የእንጨት ማገዶን በመተካት ወይም አጠቃቀሙን በመቀነስ ውጤታማ የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎችን መጠቀም የሴቶችን ሙበት የሚያከብሩና የሚጠቅሙ የተለዩ ውጤቶችን ያስገኛል። በፕሮግራሙ ንድፍ እንደታሰበው ከዘላቂ የልማት ግብ 5 (SDG 5) ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ለማሟላት፣ በእያንዳንዱ የአካባቢ ባለድርሻ አካላት ምክክር (LSC) ወቅት ለግለሰቦች የሚገኙ ጥቅሞችና ከፕሮጀክቱ በፊት ያለው መሠረታዊ ሁኔታ ግምገማ መቅረብ አለባቸው።

መርህ 3፡ የማኅበረሰብ ጤናና ደኅንነት፦ ፕሮጀክቱ በማኅበረሰቡ ጤና ላይ እውነተኛ ወይም እንደሚኖር የሚታሰብ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አይጠበቅም። CME በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውስጥ፣ በየፕሮጀክቱ የአካባቢ ባለድርሻ አካላት ምክክር (LSC) እና በፕሮጀክት ንድፍ ሰነዶች አማካይነት፣ ከጤናና ደኅንነት ጋር የተያያዙ የሥራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ሁሉም የጥበቃ መስፈርቶች መከበራቸው መገለጹንና ለባለድርሻ አካላት መግለጹን ማረጋገጥ አለበት። ይህም ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም በተቀጠሩ ሰዎች ጤናና ደኅንነት ላይ የሚያተኩሩ ግምገማዎችን ያካትታል።

መርህ 4፡ የባህል ሐብት፣ የነባር ሕዝቦች መብቶች፣ መፈናቀል እና መልሶ ማቋቋም፦

ፕሮጀክቱ ተንቀሳቃሽ የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎችን በማሰራጨት የሚተገበር በመሆኑ፣ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም በማንኛውም የባህል ቅርስ ቦታ ላይ ተጽዕኖ የማሳደር አደጋ የለውም። CME ሁሉም ፕሮጀክቶች ይህንን መስፈርት የሚያከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥና በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ደረጃ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ስለ ፕሮጀክቱ የጥበቃ መስፈርቶች በተለይም የሚከተሉትን ለመጠበቅ ስለሚደረጉ እርምጃዎች ማሳወቅ አለበት፦

• ከፍተኛ የባህልና የታሪክ ቅርስ ዋጋ ያላቸው ቦታዎችን፣ ቁሳቁሶችን ወይም መዋቅሮችን ከመቀየር፣ ከመጉዳት ወይም ከማስወገድ መጠበቅ፤

• ከግዳጅ ማስለቀቅና ከማፈናቀል መጠበቅ፤

• የመሬት ይዞታና ሌሎች መብቶችን ማክበር፤

• የአገር በቀል ሕዝቦችን መብቶች ማክበር።

መርህ 5፡ ሙስና፦ CME በፕሮግራሙ የሥራ ዘመን በሙሉ በማንኛውም ፕሮጀክት አፈጻጸም ወቅት ሙስናንና ማንኛውንም ዓይነት የሙስና ተግባር በፍጹም እንደማይታገስ ማረጋገጥ አለበት። ሁሉም ፕሮጀክቶችም ይህንን መርህ መተግበራቸውን ማሳየትና ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

መርህ 6፡ ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች፡- CME በግዳጅ የሚያሠራ ወይም ዓለም አቀፍና ብሔራዊ የሠራተኛ ሕጎችን የሚጥሱ የቅጥር አሠራሮችን የሚከተል ማንኛውንም ፕሮጀክት በፕሮግራሙ ውስጥ መካተቱን አይታገስም። እያንዳንዱ ፕሮጀክት በመርህ 6 እና በጥቅ መርሆዎች መስፈርቶች የተቀመጡትን ሁሉንም የጥቅ እርምጃዎች መተግበሩንና መስፈርቶቹን ማክበሩን ማሳየትና ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅ አለበት።

የአካባቢ እና የብዝሐ-ሕይወት መርሆዎች

መርህ 7፡ የአየር ንብረት እና ኃይል

• **የልቀት ቅነሳ፡-** ፕሮጀክቱ እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ጊዜ ውስጥ (የፕሮግራሙ የሥራ ዘመን) ከመሠረታዊ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር የአረንጓዴ ሐውስ ጋዞች (GHGs) ልቀትን ይቀንሳል። የፕሮጀክቱን ምድጃዎች መጠቀም ብዙ ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድ (CO_2) ወደ ከባቢ አየር እንዳይለቀቅ ይረዳል።

• **የኃይል አቅርቦት፡-** የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ አነስተኛ መጠን ታዳሽ ያልሆነ ባዮማስ (ማገዶ) የሚጠቀሙ የተሻሻሉ ምድጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ስለሆነም፣ ከመሠረታዊ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ከተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰበሰበው የእንጨት ማገዶ መጠን ይቀንሳል።

መርህ 8፡ ውሃ

• **በተፈጥሯዊ የውኃ አቅጣጫና ፍሰት ላይ የሚኖር ተጽዕኖ፡-** ፕሮጀክቱ በክልሉ የውኃ ሀብቶች ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖ አያሳድርም። ቤተሰቦች ለፍጆታ የሚያገኙት የውኃ መጠንም ጉልህ ለውጥ አይኖረውም።

• **የአፈር መሸርሸር፡-** ፕሮጀክቱ የማገዶ እንጨት ፍጆታን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ የተፈጥሮ የደን ሽፋንን ይጠብቃል። በዚህም የአፈር መሸርሸር አደጋን በተዘዋዋሪ ይቀንሳል፤ የውኃ ሥርዓት መረጋጋትንም ያጠናክራል።

መርህ 9፡ የአካባቢ ሐብት፣ ብዝሐ-ሕይወት እና የመሬት አጠቃቀም

• **የመሬት ገጽታ ለውጥና አፈር፡-** በፕሮጀክቱ ሥር ምንም ዓይነት ሰብል ወይም ሌላ ምርት አይመረትም።

• **ለተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭነት፡-** ፕሮጀክቱ በተፈጥሮ አደጋዎች ላይ ምንም ተጽዕኖ አያሳድርም። የመሬት አጠቃቀም ለውጥ አያስከትልም፤ በፕሮጀክቱ አካባቢ ባለው መሬት ላይም ምንም ተጽዕኖ አይኖረውም። ስለሆነም በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ ተግባራት የሚከሰቱ አደጋዎችን የማባባስ ሁኔታ አይጠበቅም።

• **ባዮሴፍቲና የዘረመል ሀብቶች፡-** በፕሮጀክቱ ውስጥ በዘረመል የተሻሻሉ ፍጥረታትን (GMOs) አይጠቀሙም።

• **የብክለት ልቀት፡-** በፕሮጀክቱ ተግባራት ምክንያት የማገዶ እንጨት ፍጆታ ይቀንሳል፤ በተጨማሪም የቅሪተ አካል ነዳጅ (Fossil Fuel) እንደማይቃጠል ይጠበቃል። ስለሆነም ብክለቶች ወደ አካባቢ የመለቀቅ አደጋ የለም።

• **አደገኛና አደገኛ ያልሆኑ ቆሻሻዎች፡-** የምግብ ማብሰያ ምድጃዎቹ በኬንያ በሚገኘው የBURN የራሱ ፋብሪካ ውስጥ የሚመረቱ ሲሆን፣ የኬንያን የጤና፣ የደኅንነትና የአካባቢ ጥበቃ ደንቦች ያከብራሉ። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚከናወኑት የፕሮጀክቱ ተግባራት በአካባቢው በተቀጠሩ ሠራተኞች አማካይነት በስርጭት፣ በሽያጭ፣ በጥገናና በክትትል ሥራዎች ላይ ብቻ የተገደቡ ናቸው። እነዚህ ተግባራትም አነስተኛ መጠን ያለው አደገኛ ያልሆነ ቆሻሻ (የማሸጊያ ቁሳቁሶች፣ የተተኩ መለዋወጫ ክፍሎችና የተበላሹ ምድጃዎች) ብቻ ያመነጫሉ። ይህ ቆሻሻም ጥገናን፣ እንደገና መጠቀምንና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን (Recycling) ቅድሚያ በሚሰጠው የፕሮጀክቱ የጥገናና የቆሻሻ አያያዝ ስትራቴጂ መሠረት ይተዳደራል። ሠራተኞችም በSDG 8 መሠረት ቆሻሻን በደኅንነት ለመያዝ ሥልጠና ያገኛሉ፤ አስፈላጊውም መሣሪያ ይቀርብላቸዋል።

• **ፀረ-ተባይ መድኃኒቶችና ማዳበሪያዎች፡-** ፕሮጀክቱ ፀረ-ተባይ መድኃኒቶችንና ማዳበሪያዎችን መጠቀምን አያካትትም።

• **የደን ሀብት አጠቃቀም፡-** ፕሮጀክቱ የማገዶ እንጨት ፍላጎትን ይቀንሳል፤ በዚህም ከደኖች የሚሰበሰበውን የእንጨት መጠን ይቀንሳል። ስለሆነም ፕሮጀክቱ የደን ሽፋንን በመጠበቅ ረገድ አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው።

• **የምግብ ዋስትና፡-** ፕሮጀክቱ በምግብ ምርት ወይም በምግብ ጥራት ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።

• **የእንስሳት ደኅንነት፡-** ፕሮጀክቱ የእንስሳት እርባታን አያካትትም።

• **ከፍተኛ የጥቅ ዋጋ ያላቸው አካባቢዎችና ወሳኝ መኖሪያ ሥፍራዎች፡-** እያንዳንዱ ፕሮጀክት ወሳኝ መኖሪያ ሥፍራዎችንና ብዝኃ ሕይወትን በተመለከተ የተቀመጡ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ፕሮቶኮሎችን የሚያከብር መሆኑንና ተገቢውን የጥቅ እርምጃዎች የሚተገብር መሆኑን ማሳየት አለበት።

• **ለመጥፋት የተጋለጡ ዝርያዎች፡-** ፕሮጀክቱ በነባር ቤተሰቦች ላይ ብቻ የሚያተኩር በመሆኑ፣ ለመጥፋት የተጋለጡ ዝርያዎችን መኖሪያ ሥፍራዎች ላይ ምንም ተጽዕኖ እንደማያሳድር ይጠበቃል።

• **ወራሪ የባዕድ ዝርያዎች፡-** ፕሮጀክቱ ምንም ዓይነት ወራሪ የባዕድ ዝርያዎችን ወደ አካባቢው አያስገባም።


burn
life · saving · stoves


burn
life · saving · stoves


burn
life · saving · stoves

Amharic Version


burn
life · saving · stoves


burn
life · saving · stoves